NAFYAD SCHOOL

2 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 BIOLOGY 2

መመሪያ አንድ ፦ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ/ሺ

1. ከጥምር ማይክሮስኮፕ ክፍሎች ውስጥ በመድረኩ ውስጥ የሚያልፈውን የብረሀን መጠን የሚመጥነው የቱ ነው

   A. መስታወት B. ድልሺ C. የአይን ምስሪት D. መሰረት

2. በእፅዋትና በእንስሳት ህዋስ ውስጥ የሚገኝ ክፍለ ህዋስ የቱ ነው።

   A. ህዋስ ክርታስ B. ፊኝት C. አረንጓቀፍ D. ህዋስ ግንብ

3. የባለ አንድ ግርባብ እፅዋት ባህሪይ የሆነው የቱ ነው?

   A. የመልካ አበባ ብዛት 3 ወይም የ 3 ብዜት ናቸው።

   B. መረብ ስርወት

   C. የመጓጓዣ ሁበረ ህዋስ በክብ መልክ ይገኛል

   D. የመልከ አበባ ብዛት 4/5 ወይም የእነዚህ ብዜቶች ናቸው

4. ከወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ውፀት እንዳይፈጠር በማድረግ ያልተፈለገ እርግዝና የሚከላከለው የቱ

   ነው?

   A. የማህፀን ቆብ

   B. ፒልስ

   C. ሉፕ

   D. ኮንደም

5. ከሴት አባላተ ወሊድ ክፍሎች ውስጥ ውህድ ህዋስ የሚፈጠርበት ቦታ የቱ ነው ?

   A. እንቁልጢ B. ቦየ እንቁልጢ C. ማህፀን D. ከረቤዛ

6. ከፓራማስየም መዋቅሮች ውስጥ ተዋልዶን የሚቆጣጠረው የቱ ነው?

A. ትንሽ ኦክለስ B. ምስለ አፍ ክፍተት C. ቤተ-ህዋስ D. ትልቅ ኦክለስ

7. ኢዩግሊናን ከእፅዋት ጋር የሚያመሳስላት መዋቅር የቱ ነው ?

A. ተኮማታሪ ፊኝት B. አረንጓቀፍ C. ልምጭት D.የአይን ነጥብ

8. በአበባማ እፅዋት ዖታዊ የመራቦ ሂደት ውስጥ ከፅንሰት በኃላ እንቁልጢ ወደ -------- ያድጋል።

A. ዘር B. ፍሬ C. ቅጠል D. አበባ

9. የፕሮቲን ልመት የሚካሄድበት የአመንጥጊ እንስሳት ከርስ ክፍል የቱ ነው?

A. ሩመን B. አቦማሳም C. ኦማሳም D. ሬቲኩለም

10. በህይወት አልባ ውጫዊ አካል ላይ የሚገኙትን ጀርሞች ለማጥፋት የሚያገለግለው የቱ ነው?

A. አንቲሴፕቲክስ B. ዲስ ኢንፌክታንት C. ማሪዋና D. ሄሮይን

11. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ለህዋስ የሚያስፈልገውን ሀይል የሚያመርት የቱ ነው?

A. ሀይለ ህዋስ B. መካነ ፕሮቲን C. ጎልጂ ዕቃ D. ህዋስ ሰፍሰልት

12. በፈሳሽ ውስጥ የሚገኙትን ቅንጣጢቶች ለይቶ ለማውጣት የሚጠቅመው መሳሪያ የቱ ነው?

A. ፍሬዘር B. ኢንኩቤተር C. ሴንትሪ ፉጅ D. ሪፍሪጅሬተርስ

13. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የአፍንጫ ፣የምግብ ቱቦዎች፣የጉሮሮን ውስጣዊ ክፍሎች የሚሸፍን

የእንሰሳት ሁበረህዋስ የቱ ነው?

A. የጡንቻ ህብረህዋስ B. የነርቭ ህብረ ህዋስ

C. የደም ሁበረ ህዋስ D. ተከላካይ ሁበረ ህዋስ

14. ከሚከተሉት የመገጣጠሚያ አይነቶች ውስጥ የመጠምዘዝ እንቅስቃሴን ለማከናወን የሚያስችለው

መጋጠሚያ የቱ ነው?

A. የዝርግ መጋጠሚያ
B. ታጣፊ መጋጠሚያ
C. የመሐል መጋጠሚያ
D. ድቡልቡል እና ሶኬት መጋጠሚያ

15. የስርአተ አፅም አካል ክፍሎች ሆኖ የማጭዴ አጥንት እና የብራኳ አጥንት በውስጡ የሚያቅፈው የትኛው ነው?

A. ፕክቶራል ግርድል B. ፔልቪክ ግርድል

C. ውስጣዊ ስርአተ አፅም D. ውጫዊ ስርዓተ አፅም

16. የሀር ትል ዑደት ህይወትን አስመልክቶ ትክክለኛውን ቅደም ተከተል የያዘው ፊደል የቱ ነው?


A. እጭ → እንቁላል → ሙሽሬ → ጉልምስ


B. እጭ → ሙሽሬ → እንቁላል → ጉልምስ

C. እንቁላል → እጭ → ሙሽሬ → ጉልምስ

D. እንቁላል → ሙሽሬ → ጉልምስ → እጭ

ከ 17-18 ያሉትን ጥያቄዎች ከዚህ በታች በሚገኘው የእፅዋት ህዋስ እና የእንስሳት ህዋሰ ስዕል ላይ ይመሰረታል





17. በ‹‹2›› ቁጥር የተመለከተው መዋቅር ምንን ያሳያል?

A. ህዋስ ክርስታስ B. ቤተ ህዋስ C. ኑክለስ D. ሁሉም መልስ ናቸው

18. ህዋስ ክርስታስ የሚያመለክተው በስንት ቁጥር የተመለከተ ነው?

A. 2 B. 1 C. 3 D. መልስ የለም

19. የተሳሰረ የምግብ ግንኙነት ሆኖ ሀይል ከአምራቾች ወደ ተመጋቢዎች መተላለፍን የሚያሳይ የምግብ ግንኙነት የትኛው ነው?

A. የምግብ ሰንሰለት

B. ውስብስብ የምግብ ሰንሰለት

C. የምግብ ደረጃ

D. ሁሉም መልስ ናቸው

20. ከንብ ዕጢዎች የሚመነጭ ሆኖ የማር እንጀራን ለመስራት የሚያገለግለው ከሚከተሉት የቱ ነው?

A. አንጋሽ ወለላ B. ሰም C. ፕሮፖሊስ D. ሁሉም መልስ ናቸው

21. ከእፅዋት ህብረ ህዋስ ውስጥ ተግባሩ በቅጠል ውስጥ የተዘጋጀውን ምግብ ወደ ስሮች እና ግንድ

ማስተላለፍ የሆነው የቱ ነው?

A. ሽፋን ጎብረ ህዋስ B. ምግብ ሽንዳ C. ዋሽንዳ D. አጣማሪ ህብረ ህዋስ

22. ከውሃዊ ምቹጌዎች በብዛት ጨው ያለው የቱ ነው?

A. ሐይቅ B. ባህር C. ኩሬ D.ወንዝ

23. የግልኮስ ሞሌኪዩላዊ ቀመር --------- ነው።

A. $C_6H_{12}O_6$ B. $C_3H_6O_3$ C. $C_{12}H_{22}O_{12}$ D. $C_5H_{10}O_5$

24. የፕሮቱን ንጥረ ምግብ የመጨረሻ ልመት ውጤት ውህድ የሆነው የትኛው ነው?

A. ግሉኮስ B. ስብ አሲድ እና ግላይስሮል C. አሚኖ አሲዶች D. ሁሉም

25. ከሚከተሉት የሰው ልጅ የፅድኛ አካል ያልሆነው የቱ ነው?

A. ቆዳ B. ሳንባ C. ልብ D. ኩላሊት

26. ከሚከተሉት ውስጥ በአረንጓዴ እፅዋቶች ምግብ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የማይረዳው የትኛው ነው?

A. ኦክስጅን B. አረንጓዴ ሀመልማል C. ካርቦንዳይኦክሳይድ D. ውሃ

27. በአንድ አካባቢ በአንድነት የሚኖሩ ህይወት ያላቸው ነገሮች እርስ በርሳቸው እና ከአካባቢያቸው ጋር

የሚያደርጉት መስተጋብር ምን ይባላል?

A. ስነ- ምህዳር B.ባዮስፊር C. ሲምባዮሲስ D. ሁሉም

28. በጋራማድነት እንስሳትና እንስሳት መካከል በሚያረገው ግንኙነት።

A. ሁለቱም ተጠቀማሉ

B. አንዱ ተጠቃሚ ሌላኛው ተጠቃሚም ተጎጂም አይደለም

C. አንዱ ተጠቃሚ ሌላቸው ተጎጂ ይሆናል።

D. ሁለቱም ተጠቃሚም ተጎጅም አይሆኑም

29. ስለ አፈር የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ ምን ይባላል።

A. ፔዳጎጂ B. ፔዶሎጂ C. ኢኮሎጂ D. ዚኦሎጂ

30. የአሸዋማ አፈር ደቃቅ እኦሶች ምን ያህል ናቸው?

A. ከ 0.002 ሚ.ሜ በታች B. ከ 0.2-2 ሚ.ሜ C. ከ 0.002- 0.2 ሚ.ሜ D. A እና B

31. ከባዮሎጂ ዘርፍ ውስጥ ስለ እንሰሳት የሚያጠናው የቱ ነው?

A. ቦታኒ B. ስነ-ህዋስ C. ዚኦሎጂ D. ማይክሮ ባዮሎጂ

32. ከሚከተሉት ውስጥ የመሀል ስርአት አፅም አጥንት ክፍል የሆነው የቱ ነው?

A. አፅመ ጭን B. የራስ ቅል C. አፅመ እግር ጣት D. ቁርጭምጭሚት

33. አረንጓዴ ተክሎች ከውስጣቸው ውሃን በተን መልክ ወደ አካባቢ አየር የሚለቁበት ሂደት ----

ይባላል።

A. ሰብሊሜሽን B. ትራንስፓይሬሽን C. የተን መሰብሰብ D.መትነን

34. ዘአካል እና የመንቀሳቀሻ መዋቅሩ በትክክል የተጣመረው የቱ ነው?

A. ኢዩግሊና ሽፋሽፍት B. ፓራማስየም -ልምጭት C. አሜባ -ሀሰረተ እግር D. A እና B

35. ከሚከተሉት ውስጥ ከፊል ልውጠተ ቅርፅ የሚያካሂደው ሶስት አፅቄ የትኛው ነው?

A. የሀር ትል B. አንበጣ C. ቢራቢሮ D. ዝንብ

36. በአንድ ምቹጌ ውስጥ የሚኖሩ የአንድ ብቸኛ ዝርያ ዘአካላት ስብስብ ------ ይባላል።

A. እዝበት B. ዘውግ C. ስርአተ ምህዳር D. ባዮስፊር

37. ከእርሻ ኬሚካሎች ውስጥ ፀረ- ሶስት አፅቄ የሆነው የቱ ነው?

A. አትራዝን B. ዴልታሜትሪን C. ዳፕ D.ዩሪያ

38. የብርሃን አስተፃምሮ በአብዛኛው የሚካሄድበት ቦታ ነው?

A. ሰፍነጌ መሀል ቅጠል B. የቅርፊ ገበር ህዋስ C. ሰግጥ መሀል ቅጠል D. ዙብ ህዋስ

39. የእንሰሳት የጉልበት በሽታ ትል ተሸካሚ ------ነው።

A.ትራፓኖስማ B. ፋሽዮላሄፓቲካ C. ቀንድ አውጣ D. የቆላ ዝንብ

ከ 40-41 ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በተሰጠው የምግብ ሰንሰለት ላይ በመመርኮዝ መልሱ

ሳር ⟶ አይጥ ⟶ እባብ ⟶ ጭልፊት

40. ከላይ በተሰጠው የምግብ ሰንሰለት ውስጥ ሳር፡-

A.አንደኛ ደረጃ ፊጂ B. ሁለተኛ የምግብ ደረጃ C. አምራች D. A እና B

41. ከላይ በተሰጠው የምግብ ሰንሰለት ውስጥ 2 ኛ ደረጃ ፊጂ የሆነው የቱ ነው?

A. ጭልፊት B. አይጥ C. እባብ D. ሳር

42. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የወንድ ዘር ዖታ ሆርሞን የሆነው የቱ ነው?

A. ፕሮጀስትሮን B. ኢስትሮጂን C. ቴስቴስትሮን D. A እና C

43.ከሚከተሉት ውስጥ አይገዜ ጡንቻ የሆነው የቱ ነው?

A.የልብ ጡንቻ B. የእጅ ጡንቻ C. የሽልምልም ጡንቻ D. ሁሉም መልስ ናቸው

44. ጠንካራው እና ውጫዊ የጥርስ ክፍልን የሚሸፍን የጥርስ ክፍል ምን ይባላል?

A. ዴንታይን B. ኢናሜል C. የፐልፕ ዋሻ D. ስር

45. ከቅጠል መዋቅሮች ውስጥ ሰቁረ ቅጠልን በመክፈት እና በመዝጋት የሚቆጣጠረው የቱ ነው?

A. ዘብ ህዋስ B. ሰፍነጌ ህዋስ C. ሰግጠ መሐል ህዋሳት D. መሐል ድራብ

46. አንድን የእፅ አካል ከሌላ የእፅ አካል ጋር በማያያዝ እንደ አንድ ተክል እንዲያድጉ የማድረግ ዘዴ ምን

ይባላል?

A.መሬት ማስያዝ B. መክተብ C. ግንድ መቁረጥ D. ራይ ዘይድ

47. ከአበባማ እፅዋት አካል ክፍል ውስጥ በአርካቢዎች ርክበ ብናኝን ለማከናወን የሚረዳው የቱ ነው?

A. ወንዴ ፅጌ B. ግንደ አበባ C. መልከ አበባ D. አበባ አቃፊ

48. ከሚከተሉት ውስጥ ለዘር ጉንቆላ አስፈላጊ የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

A. ውሀና አፈር B. ኦክስጅን፣ ውሃና አፈር

C. ውሃ ፣የፀሀይ ብርሀንና መጠነ ሙቀት D. ኦክስጅን ፣ውሃና መጠነ ሙቀት

49. ከሚከተሉት ውስጥ ቱቦ አልባ እጢ የሆነው የቱ ነው?

A. የእምባ እጢ B. የምራቅ እጢ C. የላብ እጢ D. የታይሮይድ እጢ

50. ከአንጎል ክፍሎች ውስጥ የሰውነታችንን ሚዛን ለመጠበቅ የሚያገለግለው የቱ ነው?

A. ሰረብረም B. ሰረብለም C. ሚዱላ ኦብሎንጋታ D. ሁበለሰረሰር

51. ባዮሎጂ በልማት ውስጥ ያለውን ድርሻ አስመልክቶ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

A. የጤና አገልግሎት B. የእርሻ ምርትን ለማሻሻል

C. የምግብ ምርትን ለማሻሻል D. ሁሉም መልስ ናቸው

52. ህዋስን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A. ሁሉም ህዋሶች በባዶ አይን አይታዩም

B. አብዛኞቹ ህዋሶች በመጠን ትንሽ ናቸው።

C. ህዋሳት የዘአካላት መሰረታዊ መዋቅርና ተግባር አሀድ ናቸው

D. ህዋሶች የመጡት በፊት ከነበሩ ህዋሶች ነው

53. የባለብዙ ህዋስ ዘአካል የአደረጃጀት ደረጃን አስመልክቶ ትክክል የሆነው የቱ ነው ?

A. ሁበረ ህዋስ → ህዋስ → አባል አካል → ዘአካል → ስርአተ አባል አካል

B. ስርአተ አባል አከል → አባል አካል → ዘአካል → ህዋስ → ሁበረ ህዋስ

C. ህዋስ → አባል አካል → ሁበረ ህዋስ → ስርአተ አባል አካል → ዘአካል

D. ህዋስ → ሁበረ ህዋስ → አባል አካል → ስርአተ አባል አካል → ዘአካል

54. $\frac{0233}{1233}$ የጥርስ ቀመር ያለው አጥቢ እንሰሳ አጠቃላይ የትርስ ብዛቱ ስንት ነው ?

A. 17 B. 34 C. 42 D. 24

55. ከሚከተሉት ውስጥ የሴቶች ኢመሰረታዊ መፍልኤ ዖታ ባህሪ የሆነው የቱ ነው ?

A. ፂም ማብቀል B. የድምፅ መጎርነን C. የወንድ ዘር ፍሬ ማዘጋጀት D. እንቁላል ማዘጋጀት

56. ከሴት አባላተ ወሊድ ጤና ጋር የተያያዘው ችግር የቱ ነው?

A. ያለእድሜ ጋብቻ B. የሴት ልጅ ግርዛት C. አስገድዶ መድፈር D. ሁሉም መልስ ናቸው

57. ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A. በቫይረስ ይተላለፋል B. ወጣቶችን ብቻ ያጠቃል

C. በስለታማ ነገሮች ይተላለፋል D. የሰውነትን በሽታ የመከላከል አቅም ይቀንሳል

58. እፅዋትን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

A. ኢዩካርዮቲክ ህዋስ አላቸው B. ባለ ብዙ ህዋስ ናቸው

C. በብርሃን አስተፃምሮ ሂደት ምግባቸውን ያዘጋጃሉ D. ፕሮካርዮቲክ ህዋስ አላቸው

59. ከሚከተሉት ውስጥ አበባማ እፅዋት የሆነው የቱ ነው?

A. ባህር ዛፍ B. ሰረንስት C. ጥድ D. ፈርን

60. በሀይል ፒራሚድ ውስጥ ከአንድ ዘአካል ወደ ሌላ ዘአካል የሚተላለፈው የሀይል መጠን ------

A. እየቀነሰ ይሔዳል B. እየጨመረ ይሔዳል

C. በእኩል መጠን ይተላለፋል D. የሚተላለፍ የሀይል መጠን አይኖርም

CD

CD

11

CD

BCD